# ኢሕአፓ

# ሰላም

# ቋት እንዲሞላ!

ሐምሌ 1982

በ"ፍኖተ ዴሞክራሲ" ሬዲዮ በተከታታይ የተላለፈ

ሐምሌ 1982 ዓ.ም.

# ሰላም ቋት እንዲመጣ!

የሰላሙ ፍለጋ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: አትላንታ ተፈለገች፤ ሮም ተፈለገች፤ ናይሮቢ ተፈለገች፤.... አሁንም አልተገኘችም:: ስለመገኘቷ ገራ ቀኙ የየራሳቸውን ምክንያት ያቀርባሉ:: "የናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ" ከሚለው ዓይነት ምክንያታቸው ባሻገር ገን ሁለቱም ወገኖች ዓልመው የተነሡባቸውን ገቦች ከምሉ ኅይል በተለያየ ደረጃ መትተዋል ማለት የሚቻል ነው::

ፋሺስታዊው መንግሥት በመላው ዓለም ሕዝብ ፊት እንደ ጥራቅ እንደ መቅሠፍት መታየቱ እንዲቀርለትና በሰማዩ፣ ዕርቅ ፈላጊ፣ የዋኅ ርገብ መስሉ ለዘበ፣ ለስልቦ መቅረቡ አስፈልጎታል:: እንደ ወትሮው የደነደነ ጪንቃ የለውም:: ዕብሪቱን የከቡለት፣ ጡንቻውን ያፈረጠሙለት ምግዚተኞቹ ሶቪየት ኅብረትና ጆርጀ "ከራስ በላይ ነፋስ" ብለው፣ የየራሳቸውን ጓዳ ለማስተናበር፣ አጅህን አጨጣ ብለው ከጀርባው መስስ በማለት ከሩቅ ታዛቢያች ተራ ገብተው አጀብ! አጀብ! እያሉ ነው:: በጉዳፈቻ የሚቀበለው ለማገኘት ራሱን ገብረ ገብ አድርጎ፣ አስማምቶ፣ በል የተባለውን ሁሉ ብሉ ያመነውን ከደ ከመቀረብ ሌላ ምርጫ እኒያ "ታዳጊያቹ" አልተውለትም:: አውስሰ ሜዳ ላይ ብቻውን ጉም ብሉ እንደመቅረቱ መጠን እንደወትሮው ልገስል ቢል የሚሆንለት አይሆንም:: ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ፋታ አስፈልጎታል:

ለህልውናው መሠረትም ምክንያት የሆነው ወታደራዊ ኃይሉ እንደ ረጅም ጊዜ ምኞቱ እንኳንስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዓር አስከዓር አርገጥ ጭብጥ አድርጎ ከአገሩ በታች ሊያስገዛለት ይቅርና ለራሱ የሚረገጠው ሙዱርም የበሬ ገንባር አየሆነ በመጣበት ሰዓት የሰላም ያለህ ብሎ መጮሁ የሚጠበቅ ሞኝነት ወይም ጨለሌነት ከመሆን አያልፍም:: የሰውን ልጅ ሰብአዊ መብት በማክበር ማንም ማን የማያማው ራሱንም በዚህ ከበር ጉዳይ ላይ የማይጠረጥረው፣ አስከዛሬይቱ የጥንቀት ሰዓት ድረስ መብታቸውን ገደብ ብዙ ሥቃይ በደል ሲያደርስባቸው የነበረትን ኢትዮጵያውያን ቤተ አሠራኤሎች በሰብአዊ መብት ሽፋን ከአሠራኤል መንግሥት ጋር አስከመዋዋል ድረስ ራሱን ታሪክ ከኩነናቸው ፈንጋዮች በታች ያወረደ ይህ መንግሥት፣ በሰላም ልነገድ ብሎ ቢነካ ሊያስደንቅ አይገባም::

እነሆም ንገዱ ደራ:: ትላንት ከመጤፍ ያልቆጠራቸው፣ እንደጋይል ሊያዩቃቸው ያልፈለገ፣ የትም የማይደርሱ፣ አፍኝ የማይሞሉ ቅጥረኛ ወንበዴዎች እያለ ሲያብጠለጥላቸው የነበሩት ከመቅጽበት ደረጃቸው ከፍ ብሎ እንደ እቻ ታውቀው "ተቃዋሚ ወገኖች" በሚል ስያሜ ተሞካሽተው ውይይቱ ተጀመረ:: በሰላም የተጠማው ሕዝብ የምሩን ማለለ፣ በተሥፋም ጠበቀ፣ ዓለምም ጓጓ:: የሰላም መለከት ከጽንፍ እስከ አጽናፍ ተነፋ:: ታዲያም ሁሉም ወገኖች የሰላም ጠቋርያት ተብለው ሀገረ ስበከታቸውን ሠፋ ለማድረግ፣ በዓለም አቀፍ መድረክ

.../

ላይ ምግሥ ለመቀዳጀት፣ ዕውቅናን ለማትረፍ፣ ፋታ ለማግኘት... ወዘተ. ሁሉም እንደየፍጥርጥራቸው የኹትን ያህል፣ ሰላምን ፍለጋ፣ በሰላም በምትገኝበት መንገድ አንዷት ጋት ለመራመድ አገራቸውን አንዷች ብለው አላነሡም::

ጥንታዊ ባህልና ወግ ካላት ኩሩ ከሆነችና ገበናዋን ከታች ከሆነች ሀገር የተፈጠሩ ወገኖች ባሕር ማዶ ድረስ የትየለሌ ሂደው ስሙ ጥር በዕዳን ሸምጋዮች አስከመፈለግ ድረስ መሄዳቸው መቼም ነውር ነው ባይባልም፣ በተለይ ሰላምን ፍለጋው ከምር፣ ከአንጀት ያለመሆኑ ሲደመርበት ከነሱ አልፎ እነሱንም ያበቀለችውን ሀገር የሚያስገምት ነው::

"ሳም ባልዋለበት አበት ለቀማ" የሆነው የሰላም ፍለጋ የየዋኅንን-ልብ ከመስቀል፣ ገላጋዮችን ከማድከም አልፎ ብሎ የሚራመድ ባለመሆኑ ፀደ ፍሬ ነገሩ ባይገባ ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳይ በተባለው ቀዝማ ላይ ተወዘወዘ ተወዘወዘ እዚያው ላይ ማስረጊያው ሆነ::

ፋሺስታዊው መንግሥት፣ የኢትዮጵያ ግዛት አንድነት ፍጹም ነው፤ የኤርትራ ጥያቄ በራስ ገዝ ደረጃ መፈታት ያለበት ነው ብሎ እንደፀና፣ ሻዕቢያም፣ ጥያቄዋ የቅኝ ግዛት ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን በዚያው እንጻር መፍትሔው መታየት አለበት፤ በተባበሩት መንግሥታት ተቆጣጣሪነትም ወሳኙ ሕዝብ ይደረግበት በሚለው አቋሙ መጽናቱ እንዳለ ሆኖ፣ በሥነ ሥርዓት ነክ ጉዳዮች ላይ በተደረገው የተጓተተ ውይይት

.../

የተባበሩት መንግሥታት በታዛቢነት እንዲገኙለት ጠየቀ፤ ፋሺስታዊ መንግሥት ለመስማማቱ ተስማማ፤ ሆኖም ሻዕቢያ የተባበሩት መንግሥታት ታዛቢ ለመሆን ፈቃደኝነቱን ገልጾልኛል ቢል ፋሺስታዊው መንግሥት ደግሞ የለም ሐሰት ነው፤ በመንግሥታት መካከል እንጂ በአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ አልገባም ነው ያለው ብሎ ሸምጋዩን ጂሚ ካርተርን ባይቀር ከሻዕቢያ ጋር የቃረነ ጉንጭ አልፋ ጭቅጭቅ ውስጥ ተገባ። ለሁሉም አንዳች መግባባት ላይ ባይደረስ ቀነ ቀጠሮም ባይያዝ እንደ ተንጠለጠለ ምጽዋ በሻዕቢያ እጅ መግባቷ አንዱ እልባት ላይ ያስረፈው መሰለ።

ሕወሓትም እንዲሁ "ስም ሲጠዛጠዝ ጭራ ያዝ" እንደተባለው ይህ የድራ "የሰላም ገበያ" እንዳያመልጠው በዛቻም በምንም ብሎ ከነጂሚ ካርተር መደብር ለመድረስ ባይሆንለትም በሮም ላይ ከፋሺስታዊ መንግሥት ጋር በጣሊያን መንግሥት ሸምጋይነት ሁለት ጊዜ ለመሰብሰብ ችሏል። እዚህም ላይ ከሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች አልፎ ወደ ቁም ነገር ለመሸጋገር አልተቻለም። ሕወሓት አንዴ ጊዜ ከኢሕአዴግ ሌላ ጊዜ ኢሕዴን ከተባለ ድርጅት ጋር አብሬ ሆኜ ነው መወያየት ያለብኝ አለ። ፋሺስታዊ መንግሥትም ቀደም ሲል የተስማማነው እንደ ሕወሓትነትህ ልንነጋገር እንጂ በራስህ አምሳል የፈጠርካቸውን ድርጅት አልቀበልም፤ ቢሻው ራሱን ችሎ በግል ይቅረብ አለ።

ከዚህ በኋላ አንዱ ሌላውን የሰላም እንቅፋት እያለ መወንጀሉ የሚጠበቅ ነበርና መዘራጠጡ ቀጠለ። የሮትር ቅጽል ስሞች

.../

በታ በታቸውን ያዙ፡፡ እያንዳንዱ ወገን በገባበት የፖለቲካ ንግድ ሸኩቻ ውስጥ ያካበተውን የተጣራ ትርፉን ሊያሰላስል ይችላል፤ እጅግ የሚያሳዝነው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በላዩ ላይ የሠለጠነበት ዕድሉን የሚወስንበት ሁና፣ ሥቃዩ መዘበቻ በሰላም የጨበራ ተዝካር መሆኑ ነው፡፡

ኢሕአፓ ሰላምን በየትኛው መንገድ ተጓዞን ልናገኛት እንደምንችል ደጋግሞ ገልጿል፡፡ ታኅሣሥ 1982 በልሳኑ <u>በዲሞክራሲያ</u> "ፍኖተ-ሰላም" በሚል ርእስ ከጻፈው ውስጥ የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፤

> "... በርግጥ ሰላም የጥንት ተረት በሆነችበት ኢትዮጵያ
> ማንም ማን፣ መፍትሔ አመጣም አሰመጣም ስለ ሰላም አጀንዳ
> ይዞ መወያየቱ ብቻ እንኳ ብርቅና አዲስ ነገር ነው፡፡
> በሰላም ፍለጋው አንጻርም ኀሊናን በመኮርኮር ረገድ አስተ
> ዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል አይጠረጠርም፡፡ እዚያ ስር ግን
> ያጣል፡፡..."

<u>ዲሞክራሲያ</u> ቅጽ 15 ቁ. 3 ገጽ 2

በዚሁ ጽሑፍ ላይ ወረድ ብሉ በገጽ 3 ላይ ደግሞ ...

> " .. የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘውን ሰላም የሚያገኘው አሥፓና
> ሁለት ሶስት ድርጅቶች ተገናኝተው በመጉናበሳቸውና ይቅር ለእግ
> ዚአብሔር በመባባላቸው ሳይሆን የሕዝብን ሰላም የሚያረጋግጥ፣
> ሙሉ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታን የሚያሠፍን ሥርዓት ሲቋቋም ብቻ ነው፡፡
> ሰላምን ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ ያጠፋው፣ በድርጅቶችና በመንግሥቱ
> መካከል የተፈጠረ የግል ቁም በቀል ሳይሆን የሠፊው ሕዝብ መሠረ
> ታውያን ጥያቄዎች ባለመመለሳቸው እንጂ ነው፡፡ እነዚህን ጥያቄ
> ዎች እርቆ ሰላምን ማቅረብ አይቻልም፡፡ .."

.../

በጥር 1982 አንገብጋቢ ለሆነው የሕዝቡ መሠረታዊ የዲሞክራሲ ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡ ሰላምን አያገኙትም !

በሚል ርእስ ደግሞ ካወጣው መግለጫ ውስጥ የሚከተለውን ለአብነት እንጠቅሳለን::

"...የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት በአሥጊ ሁኔታ ላይ ወድቆ የሚገኘው ዲሞክራሲ በመጥፋቱ ለመሆኑ ለማንም ሥውር አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት የሚጠበቀው ዲሞክራሲ እውን ሲሆንና ትምክህተኝነት ተወግዶ እኩልነት ሲረጋገጥና በዚህም መሠረት ሕዝቡ እራሱ የአንድነቱ ፈላጊና ጠባቂ የሚሆንበት ሁኔታ ሲረጋገጥ ነው:: ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ግን በጦርነትና በዘመቻ፣ በኩባ ሆነ በእሥራኤል፣ በሶቭየት ህብረት ሆነ በሌላ ድጋፍ በኃይልና በፍጅት የሚመሰረት አንድነት፣ የሚገኝ ሰላም አይኖርም::

በአጭሩ ኢትዮጵያ ሀገራችን ካለችበት የቀውስ ሁኔታ ልትወጣ የምትችለው ዲሞክራሲ እውን ሲሆን ብቻ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጦ ይገኛል::

ዲሞክራሲ ስንልም የይስሙላ ምርጫ፣ የግለሰብ፣ የቡድን ወይም ግንባር ቀደም ፓርቲ አምባገነናዊነት ሳይሆን የሕዝቡ የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ የመቃወም... ወዘተ. መብቶች ተከብረው የፖለቲካ ፓርቲዎች አለምንም ገደብና እገዳ የመቋቋም መብታቸው ተከብሮ ሕዝቡ ወኪሎቹን በነፃ ምርጫ ሊወስንና በምርጫ አሸናፊ ያልሆኑትም ህጋዊ ሥርዓትን አክብረው የመቃወም መብታቸው ተጠብቆ ሲገኝ ነው::

የሕዝቡ የዲሞክራሲያዊ መብት ጉዳይ የኢትዮጵያ ህልውና [illegible] [illegible] ጉዳይ በመንግሥትና በአንድ ወይ ሁለት ድርጅቶች ድርድር የሚወሰን ሳይሆን ሕዝቡን በቀጥታ የሚመለከትና የሕዝቡንም ውሳኔ የሚጠይቅ ነው::

.../

ኢሕአፓ የሚታገለው ሕዝቡን ተከቶ ለመናገር ወይ በሥል ጣን ለመሰየም እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ገልፀ አድርጓል::

የኢሕአፓ ዓላማ በተወሰነ ክፍለሐገር ወይ ክልል በገዥ ነት ለመሰየም /ለመገንጠል/ ስላልሆነ በዚህ መልክ ከመንግሥት ጋር የሚደራደረው የለውም::

ኢሕአፓ ጊዜያዊ የፕሮፓጋንዳ ጥቅም ለማግኘት ሲል ከሕ ዝቡና ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ሳያቀናጅ በተናጠል ከመንግሥት ጋር አይደራደርም::

ኢሕአፓ የተወሰኑ አባላቱን በሚኒስትርነት ለማሾም የሚ ታገል ስላልሆነ ይህን ቀደም ሲልም ለአነመሲበን የተወውን አድርበይነት አሁንም ርኩስ ዓላማ ነው ብሎ የሚያወግዘው ነው::

ስለዚህም በሰም እንዳብፍን ከተፈለገ የኢሕአፓ ጥያቄ የሕዝቡ መሠረታዊ ጥያቄ እንጂ ከቶም ሌላ አይደለም:: የኢሕአፓ ጥያቄና ፍላጎት ሚስጥር አይደለም:: የሕዝቡ ዲሞ ክራሲያዊ መብቶች ከታወቁ፣ ከተከበሩ፣ በተግባር ከዋሉ ኢሕአፓ ሆነ ሌሎች ፓርቲዎች ህጋዊነታቸው ከተረጋገጠ፣ የሕዝቡ ነፃ ምርጫ የመንግሥቱን ዓይነት ይዞትና ፖሊሲ ወሳኝ መሆን እንዳ ለበት ከታመነ ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ በሰም፣ ለሕዝቦቿ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነትና ብልፅግና የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማ ድረግ ወደኋላ የሚል አይሆንም::

ዲሞክራሲ ከተሰመደው ደርጋዊ ትርጉምና እገዳ ተላቆ በእ ርገጥ እውን የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር ኢሕአፓ ከሌሎች ዲሞ ክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በህብረት ገንባርም ሆነ በሽግግር መንግ ሥት ለመተባበር ዝግጁነቱን ደጋግሞ ገልጧል:: አሁንም ይገል ፃል::"

ከገጽ 2 — 3

.../

በዚህች ቅጽበት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም ፊት ትልቅነቱ፣
አርቆ አስተዋይነቱ፣ በሳልነቱ፣ ሥልጣኔው የሚመዘንበት ከባድ ፈተና
ቀርቦለታል። ተማሪ ፈተና ሲወድቅ ዳግመኛ ለመፈተን ዕድል እን
ደሚሰጠው ዓይነት ከቶ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አይበለውና
አይውደቅ እንጂ ተወደቀማ በዘመናት ውስጥ፣ በተለይም ባሁኑ ጊዜ
ገዢዎቹ ያደቀቁት የሥራ አካላቱ ወድቆ ለመነሣት ያለው ጥንካሬ
የሚያስተማምን ደረጃ ላይ አይገኝም። የፈተናው ከባድነት መታ
የት ያለበት ከዚህ አንፃር ነው። ይህን ከባድ ፈተና የኢትዮ
ጵያ ሕዝብ የሚያልፈው በጭፍን ገልበጣ ወይም በገልብ ሹምደዳ አይ
ደለም። ፈተናውን የሚያልፈው ብልቱን በውል ለይቶ ወገና ሥር
ዓት ባለው መንገድ እንዳመጣጡ ተገቢውን መልስ መስጠት ሲችል ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ክብሩ የሚታወቀው፣ ስሙን የያዘው ተበ
ደልኩ የሚለው፣ የጉዳዩ ባለቤት እያለ፣ ሹማገሌ የሚሰከባቸው፣
ታረቁልን እያለ ሁሉ የሚያረገድላቸው፣ ለጉዳዩ ባዕድ ባይሆኑም
የኢትዮጵያ ሕዝብ ውክልናውን ያላሰጣቸው፣ እነሱም ሕዝቡን ሲጠይቁት
አክብርቶ የሌላቸው፣ ራሳቸውን ሥዩማን ያደረጉ ወገኖች መሆናቸው
አንዱ የፈተናው አስቸጋሪ ገጽ ነው። በአንድ በኩል ፋሺስታዊው
መንግሥት፣ በሌላው በኩል የተወሰኑ ታጋይ ኃይሎች ሁነው በዕርቅም
ሆነ በጦርነት የሚደርሱበት መፍትሔ የነዚህኑ ወገኖች የግል ፍላ
ጎት ከማሟላት፣ የሥልጣን ጥማቸውን ከማርካት አልፎ በጉዳዩ ላይ

.../

ሲመከርበት፣ ሲዘከርበት፣ ሊቃወም ሊተችበት፣ የሆዱን ቁስል ሊገል
ጽበት፣ በሽታውን ሊያባውቅበት ሳልታደለ ሕዝብ፣ በበሽታው ላይ ተው
ሳክ ከመጨመር ሌላ የሚፈይድለት ነገር የለም፡፡ ፋሺስታዊው መን
ግሥት የዕድሜ ገመዱን ከንዱም ወደማብቃቱ ላይ መሆኑ በሰንዘርና
በጋት መካከል ከርከር ቢያስነሣ እንጂ ከዚያ የሚያልፍ አይደለም፡፡
ከዚህ ተንደርድሮ ግን ጦርነት ሊያከትም ነው፤ አማን በአማን ሊሆን
ነው ብሎ ከማለም ይልቅ አንዱ የጦርነት ምዕራፍ አልፎ ሌላ አስከፊ
የሆነ በዓይነቱም የተለየ የጥንቱን የዘመነ መሣፍንት መዋዕል ያጠ
ቃስ አዲስ ምዕራፍ ሊጀመር ነው ብሎ አስደንጋጩን ዕውነታ ዓይንን
ባይሰብሩ ትክ ብሎ ተመልክቶ ያንን ምዕራፍ ለማጠፍ አእምሮን ሁለ
ንተናን አሰባስቦ እዚያ ላይ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

ፋሺስታዊው መንግሥት፣ የአገራችን ህልውና አደጋ ላይ
ወድቋልና ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ ለሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ
ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ሳለው፣ በምርኩዝ ለሚሄደው ባይቀር ጥሪ አድ
ርጓል፡፡ አደጋው የምሩን ዐይኑን አፍጥጦ መጥቷል፤ እዚህ ላይ
እውነቱን ነው፡፡ ግን አደጋውን እንዴት ነው የምንመልሰው የሚለው
ነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረበው አንዱ የፈተና ጥያቄ፡፡ ጥያቄው
የምርጫ ጥያቄ ነው፡፡

ሀ/ ሠፊው ሕዝብ ከፋሺስታዊው መንግሥት ጋር ቆሞ
ሀገሩ ስትፈርስ ማገር መምዘዝ፣ ወይስ?

.../

ለ/ ሠፊው ሕዝብ ራሱን ችሎ የሕዝቦችን አንድነትን ለማስጠበቅ፣ ራሱን ለመከላከል ቆርጦ መነሣት፣ ትግሉን ከዲሞክራሲያውያን ኃይሎች ጋር ማቀናጀት፤

ፋሺስታዊ መንግሥትን መንግሥት አድርጎ በኤርትራ ውስጥ ሰላም ማምጣት፣እህ ብሎ መስማት፣ የሚታሰብ ነገር አይደለም፡፡ በትግራይ፣ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በመሀል አገር፣ በዳር አገር በየትም የት የኢትዮጵያ ክልል ፋሺስታዊ መንግሥትን አስባባቢ አድርጎ፣ ሰላምን ማምጣት ሕዝቡን ለሀገሩ እንዲቆም ለማድረግ አልተቻለም፣ አይቻልምም፡፡

የኤርትራ ሕዝብ ምን ብሎ ነው አፍ ከፍቶ የሚጠየቀው? ለምልከት ይህ ተረፈ፣ ያ ዓነ በማይበልበት ደረጃ በጅምላ መንደሩ የሚጋየው ሕዝብ፣ በናፓልም የሚለበለቡት አእራግና ሕፃናት፣ አገር ነቅለው በረሐ ጥለው የሚሰደዱት ቤተሰቦች፣ በታንክ የሚደፈጠጡት፣ ዘወትር በጥይት የሚቆሰሉት አፈር ገፊዎች...ወዘተ. እነ ደሚባለው ወንበዴዎች ሁነው ተገኝተው ነውን? መንግሥቱ ኃ/ማርያም መልሶ መሳልሶ የኤርትራን ችግር የወረስነው እንጂ እኛ የፈጠርነው አይደለም ይላል፡፡ በሱ ጊዜ ሳልተፈጠረ ችግር መፍትሔው በመደዳው ሰው እንዳይተርፍ አድርጎ ሕዝብን መጨፍጨፍ ነውን? ለ30 ዓመታት ባሩድ የታጠነች ምድርን ከፋሺስታዊው መንግሥት የሚወጣ የሰላም ይሁን

.../

የፈለገው ዓይነት የተሠራ ትንፋሽ፣ ዕጣን ቢነደድ ሆኖ ያን የተበ ከለ የፖለቲካ አየር መዓዛ ይሰጠዋል ብሎ መመኘት ሞኝነት ነሆለል ነት ነው::

በትግራይ፣ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በማንኛውም የፋሺስታዊው መንግሥት ጦር በዘመተበት ሁሉ ያለንዓች ጥያቄ በጥይት የሚያጭደውን፣ እህሉን በክምር በጎተራው የሚያጋይበትን፣ በረቱን ያለ ከብትና ገር ገሙን ያለ በግ ፍየል የሚያስቀርበትን፣ ቅል ቋንቋ ሳይቀር የሚ ዘርፈውን፣ ያለጨሪ ቁብሪ ያለ ጥሪት ያለ ረዳት ያስቀረውን ሕዝብ ይህን መንግሥት መንግሥትህ ነውና ቁምስት ብሎ መናገር የሚችል አን ደበት ምን ይደፍር?

ወይስ በልዩ ልዩ መቀቅሮች እጁ አገሩ ተኩደኩዶ፣ አፉ ተለጉሞ በግዑዛን ፍጥረታት ደረጃ ወርዶ ካድሬዎች ሊጣውን የሚጋል ቡትን ያን በነሊና ቁስል ኩርምት ጭብጥ ያለ ሕይወትና ሞት ትርጉ ማቸው የተሳከረበትን ሕዝብ ነው በፋሺስታዊ መንግሥት ሥር ሰላም ታገኛለህ፣ አገር ይረጋጋል ብለን ልንደልለው የምንችለው?

ሐዘንም ደስታም በሀገር ነውና የደረሰብህን በደል ወደ ጎን ትተህ መጀመሪያ አገርህን አድን ተብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠ ይቋል:: በርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀይ ሽብር ተብሎ በነቂስ ልጆቹን ከገበረበት ጭፍጨፋ ጀምሮ ጋብ ባይል የወረደበትን ገፍ ለሀገሩ መባዕ አድርጎ ቢያቀርብ ብልጠው ነበር:: የኢትዮጵያ

ሕዝብ ላገሩ መቆም፣ ላገሩ መሞት አልጠፋውም:: በዚህ ረገድ አፍን ይዞ ፊደል የሚያስቆጥረው አይፈልገውም፤ ነገሩ ያለው ላገሩ የሚቆመው ከማን ጋር ነው? የሚለው ላይ ነው:: ፋሺስታዊው መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እንደ ቁጥኝ የሚፈራ የሚጠላ ነው፤ ቁጥኝ ተይዞ እንተቃቀፍ ማለት በጠያቂው በኩል ዓይን አውጣነት ሲሆን ለተጠያቂው ግን የሚሰቀጥጥ አንገዓ ነገር ነው:: ይልቁኖ በውድም በግድም ፋሺስታዊውን መንግሥት ተጠግተው በበሽታው የተለከፉት ወደ ሕዝቡ ቀርበው የሀገረ ሰብ መድኃኒት ቢፈልጉ ራሳቸውን ፈውሰው ልጆቻቸውንም ከውርዴነት ያድናሉ::

ሕዝባዊ መሠረት የሌለው መንግሥት ሕዝብን ሲያድን፣ ሃገርን ሊያተርፍ አይችልም:: ለአሥራ ስድስት ዓመታት የተሸከመው ወታደራዊ ቆጡ፣ ባሉቹ ነቅዘው እየተፍረገረጉ ነው:: ከመውደቅ የሚያድነው ነገር የለምና ማንም አጫፋሪ የሚሆንበት ምክንያት የለውም:: ይልቁንም መዳን የማይችለውን፣ የማይገባውንም መንግሥት ለማዳን በከንቱ ከመማሰን፣ መዳን የምትችለውንና መዳን ያለባትን ሀገር ለማዳን ያለ የሌለ ኃይልን ወደዚያ ማዞር ያስፈልጋል::

የፈተናው በጣም አስቸጋሪው ክፍል መንግሥት እየፈረሰ ባለበት ሁኔታ፣ ፋሺስታዊ መንግሥትን ምስጋን ይንሣውና የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደራጀ መልክ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር በሚችልበት ሁኔታ ላይ አለመገኘቱ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ የተደራጁት ታጋይ ኃይሎች

.../

የኢትዮጵያን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎትና አመለካከት
የሚያንፀባርቅ የጋራ ፕሮግራም ነደፈው፣ በአንድነት ሠምረው ለመ
ገኘት ካለመቻላቸውም በላይ ራሳቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደራሴ
አድርገው የዲሞክራሲ መቀነን ለሌላው ሊያወጡ የተሠለፉ፣ ሌላ
አምባገነናዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በወታደራዊ ኃይል ሊጭኑ
ያቆበቆቡ ቡድኖችም መኖራቸው ነው። እነዚሁ ወገኖች ይህ ካልሆ
ነላቸውም ልዩ ልዩ የብሔር ድርጅቶች አያሉ መፍጠራቸውን በመቀጠል
የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከአንድነታቸው ይልቅ ልዩነቶቻቸው ላይ፣ የፍ
ትሕ ርትዕ የእኩልነት ሥርዓት ወደሚመሠረትበት የብሩህ ዘመን፣ የዕ
ድገት የብልፅግና አቅጣጫ ከማትኮር ይልቅ፣ ከሕብረተሰብአዊ እድ
ገት ጋር ተያይዘው የመጡ ያለፉና ያሉም ቁስሎችን በመጫር ቁስሎቹ
እንዲነፈርቁና ሕዝቦች እርስ በርሳቸው ቂም እየተቋጠሩ በረባ ባል
ረባው እንዲናከሩ፣ ሀገር በኩርማን በኩርማን መሬት ተሸንሽና ተራ
ምዳው ወደመጣችው፣ ዘመናት ወዳለፉበት የድንቁርና ታሪክ ሊገፉት
እንደሚከጅሏቸው ፍንጮች እየታዩ ነው።

በፍትሕ ርትዕ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት የሚ
ረጋገጥበት፣ ልዩ ልዩ ፓርቲያችን የምታቅፍ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊት
ኢትዮጵያን ለመመሥረት በሀቅ የተነሡ ታጋይ ኃይሎች ቅራኔያቸቸውን
ከሀገር በፊት ባያደርጉ፣ ከማናቸውም ጥቅም በላይ የሀገራቸውን
ህልው መሆን አስቀድመው በጋራ ፕሮግራም ለመሠለፍና ከኢትዮጵያ
ሕዝብ ጎን ቆመው ሐሳቡን ለመፈጸም፣ ፈቃዱን ለመሟላት፣ አፈፍ
ብሉ በመነሣት ታጋይነታቸውንና ዲሞክራሲያዊነታቸውን፣ የሕዝብ

...../

ልዕልናን መቀበላቸውን ማስመስከሪያቸው መፈተኛቸው አሁን ነው:: ፈረሱ የረገጠው፣ ዓይኑ የፈቀደው ሁሉ የኔ ግዛት ነው በሚል የሚደረግ ሽምጥ ገልቢያ ገፋ ቢል ነፍጠኛ ደቦኝ እንደሁ ነው እንጂ የሕዝብ ድጋፍ መመዘኛ ከቶውንም አይደለም:: የሕዝብ ድጋፍ በውል በሚለካበት በፖለቲካው መስክ አስተውሎ መራመድና በሕዝቡ ውስጥ የዲሞክራሲያዊ ባህልን መሠረት ለመጣል መሥራት ያለበት ከባድና አንገብጋቢ ሥራ ላይ መረባረብ የሀቀኛ ታጋዮች ዐቢዩ ተልዕኮ ነው:: ሠፊው ሕዝብ ውስጥ ሥር ያልሰደደ፣ ከመሀሉ ያልበቀለ፣ ሕዝብ አርሞ ኮትኩቶ ያሳባደገው፣ የሕይወት እስትንፋሱን አፍ ያሳለበት የርዕዮት፣ የአስተሳሰብ፣ የዲሞክራሲ የሰላም ተክል በጊዜያት ውስጥ ጧጥቶ፣ ጠውልጎ ለሕዝብ በቀቀን ሁና ከመጥፋት በስተቀር ሲያብብ ሲያፈራ አይችልም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላምን ኩታ እንዲላበስ በእውን ከፈለገን ከሕዝብ ውስጥ የዲሞክራሲ ምድርን ገምሰን፣ ከሰከሰን፣ አለስልሰን መልካም የዲሞክራሲ ገበሬዎች ሁነን መገኘት ይኖርብናል። ከእንደዚያች ዓይነት ከለሰለሰች የዲሞክራሲ ምድር ነው የሰላም የጥጥ ፍሬ ሲበቅል፣ ሲያፈራ ሲንዠረገግ የሚችለው::

"ራሴን በራሴ አፈን በምላሴ ካላንቀሰሰጠስኩት ማን ያንቀሳቅጥስልኛል" እንደተባለው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅቢፀ ተሥፋ ውስጥ ባይገባ፣ ዕድሉን በራሱ እጁ ውስጥ ለማስገባትና ማንም እየተነሣ የሚጫወትበት ሀገሩን የራሱ አድርጎ ለመቆጀት ቁርጥ በመነሣት ከሃሊነቱንና ታላቅነቱን የሚያስመሰክርበት ጊዜ አሁን ነው:: ያለኔ የሚያውቅለት የለም ብሎ በመታበይ የተነሣ ሁሉ ኢትዮጵያን ዘንቆሉ

.../

ዘንቶሉ በሕመም ላይ ሕመም እያከለበት ለዚህ አበዛኝ ምዕራፍ አብቅቷታል፡፡ እንግዲህስ ያ፣ አታውቅም፤ የተባለው ሠፊ ሕዝብ ደግሞ ዕድል ይሰጠውና ጉዱ ይለይ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተደራጀሁም በሚል ይህን አሥጊ ሁኔታ እጅን አጣጥፍ ሊጠብቀው አይገባም፡፡

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የምትኖር ባለ—ሀገር ሕዝብ፤

ልታፈልቅ በምትችለው መንገድ፣ ልትፈጥር በምትችለው መሳ ሁሉ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ማጥበቅና በመሃሉ ነፋስ እንዳይገባበት የቅራኔ ቀዳዳዎችን በመድፈን ሕዝብን ሊያለያዩ፣ ሀገሪቱን ሊበታትኑ የተነሡ ኃይሎች አንድነትህን እንዳያናጋብህ፣ ከዚህ አደጋ ነቅተህ ለመጠበቅ፣ ሀገርህን ለማትረፍ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብሃል፡፡ ሲወርድ ሲዋረድ በቆየው ልምድህ መሠረት ሽማግሌ መርጠህ እየተላላክህ፣ እርስ በርስህ እየተጉናበስክ፣ ምክር እየተለዋወጥክ፣ አባት አያወጣህ፣ የጎበዝ አለቃ እየመደብክ አንድነትህን አስጠብቀህ፣ የአስረሽ ምቺው ሁኔታ እንዳይፈጠር፣ የነገሮችን ሂደት ተቆጣጥረህ መረጋጋትን ፈጥረህ፣ ይህችን መሪ ሰብሳቢ ያጣች ሀገር ከብከበጋይዘ፣ የመቆየት ከፍተኛ ኃላፊነት በጫንቃህ ላይ ወድቆብሃል፡፡

. . . /

በከተማና ባካባቢው በልዩ ልዩ ሙያ የተሠማራኸው ሠርቶ አደር
ሕዝብ፤

ስዚህ ውስብስብ ሁኔታ ተስማሚና አመቺ የሆነ የአደረጃ
ጀት ቅርጽ በመፍጠርና በመደራጀት ራስህንም የምታስታጥ
ቅብትን መንገድ ሁሉ ፈልገህ በመታጠቅ የቀውስ ሁኔታዎ
ችን ተቋጣጥረህ ሀገርህን በአንድነቷ ጠብቆ በማቆየት
የጋራ ዓላማ ተቆራኝተህ፤ ተገቢውን የፖለቲካ ቅኝት ይዘህ፤
ሺ ብትን ሊያደርጉህ ለሚሹ፤ በገርገሩ ሰጠቁሙ ለሚፈልጉ
ኃይላት የማትፈረከስ ጽኑ አለት ሁነህ መገኘት ያባት ዕዳ
ሁኖ መጥቶብሃል፡፡

ጭቁን ወታደር፤

ይህ ፋሽስታዊ መንግሥት፤ የሀገር አንድነት መሠረት የሆ
ነውን ሠፊ ሕዝብ መሠረታውያን መብቶችን ነፍጎ፤ የዜግ
ነት መብቱን ገፍፎ በወታደራዊ ኃይል ብቻ የሀገር አን
ድነት አመጣለሁ ብሎ በከንቱ ከአባት ሲማገድህ፤ የዐመፅ
በትሩ ሲያደርገህ ዓመታት ከቆጠረ በኋላ ይኸው ደምህን
ደመ-ከልብ አድርጎ ሀገሪቱን ከመፈራረስ አደጋ ላይ ጥሎ
እየተሰናበተ ነው፡፡ ጭቁን ወታደር ! ጎራህ ከአብራኩ
ከተከፈልከው የሠፊው ጭቁን ሕዝብ ጎራ በመሆኑ ከሚሰና
በተው ጨቋኝ ፋሽስታዊ መንግሥት ጋር ያለ ብጤትህ ወደ
ታሪክ ትቢያ ከመውደቅ ይልቅ ከሚሰነብተው፤ ከሚኖረው

.../

ሠፊው ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሁነህ ታሪክህን ለማደስና ራስህንም ነፃ ለማውጣት ይህችን ታሪካዊ ቅጽበት በብልኀነት ልትጠቀምበት ይገባል፡፡ ለዚህም ራስህን በልዩ ልዩ ዘዴ ተጠቅመህ ማደራጀትና የሠፊው ሕዝብ የትግል አካል በመሆን፣ የሕዝቦች እኩልነት የሚረጋገጥባት አንድነቷ የተጠበቀ የዕውነተኛ ዲሞክራሲና የሰላም ሀገር ለመመሥረት ሁሉንተናዊህን ለዚህ ጎሳ ከተገለሉ ሀቀና ዲሞክራሲያዊያን ኃይሎች ጋር ተግባራዊ ትብብርና ትግል ምርጫ ቀርቦልሃልና ታሪክህን ቀድሰበት፣ የሕዝብ ልጅነትህን አስመስክርበት፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በፈተና ሰዓት አንደ አንድ አካል ሁኖ የመቆምና የመመከት፣ ችግርን በጋራ የመወጣት አኩሪ ታሪክ እንዳለው የሚታበል አይደለም፡፡ ያ ታሪክ ድጋሚን ጠይቋል፡፡ ያ ታሪክ ይደገም ዘንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ባገር የለም ዋዛ" ባሉ የፋሺስቶቹን "አገር የማዳን" ቀልዱና ቅዠት ከጀርባ ባይጥፍ ራሱን በሚያመች መንገድ ሁሉ አደራጅቶና አስታጥቆ ከሁሉም በፊት ሀገሪቱን አረጋግቶ ለመያዝና አንድነቱን ሊያፋልሱ፣ ሀገሪቱን ሊያመሰቅሉ ከሚሹ ወገኖች ለመከላከል በሚችልበት ሁኔታ ራሱን ማስገኘት አለበት፡፡ ባሁኑ ሰዓት ይህን አጅግ ከባድ ሐላፊነት ለመረከብ ብቃት ያለው ራሱ ሠፊው ሕዝብ የመሆኑን ጉዳይ ዕውነታ ተቀብሉ ራሱን የትግሉ ባለቤት አድርጎ በልበ ሙሉነት መነሣትና ከጎኑ ተሠልፈው በሀቅ ለዲሞክራሲ፣ ለሰላም ለሀገርና ለሕዝብ አንድነት

.../

ከሚታገሉ ዲሞክራሲያውያን ኃይሎች ጋር ኅብረቱን አደልድሎ ሥርዓት በያዘ መንገድ ወደ ሽግግር መንግሥት የሚወስደውን ጥርጊያ መንገድ የማንጠፍ መሐንዲስነቱ አሁን ሕዝብ ላይ ወድቋል፡፡ በዚህም ጥርጊያ ተጉዞ ልዩ ልዩ የፖለቲካ አመለካከት የሚንፀባረቅበት የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ፈጥሮ የጦርነት፣ የሁከትና የልቅሶ የሰቆቃው የታሪክ ምዕራፍ የሚታጠፍበትን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም ፊት አንገቱን አቅንቶ ታላቅነቱን ታሪከኛነቱን የሚያሳይበትን ብሩኅ ፀዳል በታሪክ አድማስ ላይ መፈንጠቅ የሠፊው ሕዝብ ታሪካዊ ተልዕኮ የትውልድ አደራ ሁኖ ቀርቧል፡፡

==== /// ====

ኢሕአፓን አስመልክቶ ለሚደረጉት ማናቸውም አይነት ግንኙነቶች በሚከተሉት አድራሻዎች ይጠቀሙ_


*SPIC*
*P.O.Box 710358*
*Dallas, Texas 75371*
*USA*

*SPIC*
*46 Rui de Vaugirard*
*Paris 75006*
*France*

*SPIC*
*P.O.Bax 2688*
*Arlington, Virginia 22204*
*USA*